የአድዋ የድል በዓል 113ኛው ዓመት መታሰቢያ ቶሮንቶ ካናዳ በቅንጅት / መኢአድ ጽህፈት ቤት በልዩ ዝግጅት ታስቦ እንደተከበረ ታወቀ። በየካቲት 23 ቀን 1888 ዓም የተገኘው  የአድዋ አኩሪ ድል እንደሚታወቀው ኢትዮጵያ በዚያን ዘመን ሊወራትና ቅኝ ግዛት ሊያደርጋት የመጣውን አንድን የአውሮፓ አገር በጦርነት ድል በማድረግዋ ወራሪዋን ጣሊያንን አዋርዶ የመለሰ፣ አውሮፓን ያስደነገጠ፣ ኢትዮጵያን ደግሞ በመላው ዓለም ዝነኛና ታዋቂ ያደረጋት፡ ለአፍሪካውያን ኩራትና የነጻነት ምልክት እንድትሆን ያስቀመጣት በመሆኑ በየዓመቱ ኢትዮጵያውያን በደስታ ሲያከብሩት የቆየ ሲሆን ባለፉት ጥቂት ዓመታት ወዲህ ደግሞ በውጭ አገር የሚገኙ ኢትዮጵያውያን ማክበር ጀምረዋል።




በካናዳ የቅንጅት/መኢአድ ፅህፈት ቤትም የአድዋ 113 ኛው በዓል ታስቦ የተከበረው የኮርያው ጀግና አርበኛ የተከበሩ ሻምበል ማሞ ሀብተወልድ በአድዋ ስለተካሄደው ጦርነት የወገንና የጠላት አሰላለፍና ስለተገኘው ድል በቃል፡ በጽኁፍና በቻርት በተደገፈ ገለጻና ማብራሪያ እንዲሁም በጥያቄና መልስ ዝግጅት ያቀረቡ ሲሆን፡ የአቀራረቡ ዝግጅት የጀግኖች አባቶቻችንን ገፅታና መስዋዕትነት በዘመኑ የነበርን እስኪመስል ድረስ በግሩምና በተብራራ ሁኔታ በጽህፈት ቤቱ ለተገኙት ደጋፊዎችና አባላት አቅርበዋል።

ጽህፈት ቤቱም እንደዚህ ዓይነት ጀግና አርበኛ አባት በመካከላችን ተገኝተው የአባቶቻችን አኩሪ ታሪክ በማስረዳታቸውና በማቅረባቸው የተሰማውን ደስታና ምስጋና አቅርበዋል።